# የአርነት ጸሎት

የሰማይ አባት ሆይ እርግማን የሆነብኝን / ያስከተለብኝን/ የእኔንና የአባቶቼን ኀጢአት ይቅር እንድትለኝ ንስሐ እገባለሁ፤ ያለመታዘዛችንን፣ አመፃችንን፣ ጠማምነታችንን ፣ መተተኛነታችንን፣ የጣዖት አምልኮአችንን፣ በምኞት መንደዳችንን፣ አመንዝራነታችንን፣ በዝሙት መመላለሳችንን፣ ሌሎችን ማንጓጠጣችንን፣ ነፍሰ ገዳይነታችንን፣ ማታለላችንን፣ ውሸታምነታችንን፣ ድግምተኛነታችንን፣ መናፍስትን ማስነሳታችንን / አጋንንት ሳቢነታችንን / ሟርተኛነታችንን ሁሉ ይቅር እንድትልና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አጥበህ እንድታነጻኝ እጸልያለሁ::

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በተሰጠኝ ስልጣን በሕይወቴ ላይ የተጣበቀውን እርግማን እሰብራለሁ:: የደህንነትን፣ የመጉደልን፣ የውድመትን፣ የበሽታን፣ የሞትንና የመቅበዝበዝን እርግማን ሁሉ እሰብራለሁ፣ በትዳሬ ላይ፣ በቤተሰቤ ላይ በልጆቼ እና በማሕበራዊ ግንኙነቴ ላይ ያለውን እርግማን ሁሉ እሰብራለሁ:: የማስወገድን፣ የትዕቢትን፣ የዓመጽን፣ በምኞት የመቃጠልን፣ የቤተዘመድ ውስጥ ዝሙትን፣ በወሲብ የመደፈርን፣ የአክአብና የኤልዛቤል ሕይወት ልምምድን፣ የፍርሐት ፣ ደምፍላትን፣ በአዕምሮ በሽታ የመጃጃልን የእብደትን፣ የመምታታትን እርግማን ሁሉ እሰብራለሁ::

በገንዘቤ፣ በአእምሮዬ፣ በወሲባዊ ባህርዬ፣ በስሜቴ፣ በፈቃዴና በግንኙነቴ ላይ ያንዣበበውን እርግማን ሁሉ እሰብራለሁ::

ማንኛወም ድግምት፣ ደንቃራ ያፍዝ አደንግዝና ሌሎችንም የአንደበት መርገምትን ሁሉ ከሕይወቴ ላይ እሰብራለሁ::

የእርግማን ውጤት የሆነውን ማንኛውንም የእስራት፣ የእግረሙቅ፣ የሰንሰለት፣ የገመድ፣ የልማድ አዙሪትን ሁሉ እሰብራለሁ::

በገላ. 3:13 መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋእትነት ከሕግ እርግማን ተዋጅቻለሁ:: ስለዚህም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተሸፍኜ እመላለሳለሁ፣ እንዲሁም እኔንና ከእኔም በኋላ የሚነሱትን ዘሮቼን ሁሉ

ከእርግማን እፈታለሁ። በአባቶቼ ኀጢአት ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ይቅርታ አውጃለሁ።

ኀጢአቴ የተሰረዘልኝ ሰው ነኝና የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታዘዝና በዓመፃ ምክንያት የመጣብኝን እርግማን ሁሉ በኢየሱስ ስም እሽራለሁ። ኑዛዜ ወደ ደኅንነት ይመራናል በእምነት እመለሳለሁ። ስለዚህም የአብርሃም በረከት የእኔ እንደሆነ አምናለሁ። የተባረክሁ እንጂ የተረገምኩ አይደለሁም። ራስ እንጂ / ጅራት / አይደለሁም፣ በላይ እንጂ በታች አይደለሁም። እኔ በመውጣት ብሩክ፣ በመግባትም ብሩክ ነኝ። የተባረኩ ነኝ /ተባርኬአለሁ/ እግዚአብሔር የባረከው የተረገመ ሊሆን አይችልምና።

በኢየሱስ ክርስቶስም . . .፣ የእምቢታ፣ የቁስለት፣ መራርነት ይቅር ያለማለት፣ እስራት፣ የጭንቀት፣ የሞት፣ የውድመት፣ የፍርሐት፣ በምኞት የመንደድ፣ የጠማምነት፣ የአእምሮ ክብደት፣ የጥንቆላ፣ የድህነት ጎደሎነት ፣ የዕዳ፣ የመሳከር / የመምታታት/፣ የማመንታት፣ የበሽታ፣ የስቃይ፣ የፍቺ፣ የመለያየት፣ የሁከት፣ ያለመግባባት፣ የድንዛዜ፣ የመከፋት፣ የብቸኝነት: የሐዘንተኛነት፣ ራስን የመጥላት፣ የብስጭት፣ በቁጣ የመንደድ፣ የመብከንከን፣ የተቅበዝባዥነት፣ የመስደብ፣ የሱሰኝነት መንፈስ ሁሉ ወጥቶ እንዲሄድ አዛለሁ!!

እግዚአብሔር ሆይ በእርግማን የተነሣ ሕይወቴን መቅኖ ካሳጣው ከማንኛውም የእርኩሳን መናፍስት አሠራር ነጻ ስላወጣኸኝ አመሰግንሃለሁ።